# የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

2015 ሰኔ ቅጽ 1 ቁጥር 15

## በሲዳማ ክልል ብላቴ ዙሪያ ወረዳ በክላስተር የተደራጁ 65 አርሶ አደሮች ማሳ በበቆሎ ምርት መሸፈኑ ተገለጸ።

በሲዳማ ክልል ብላቴ ዙሪያ ወረዳ በክላስተር የተደራጁ 65 አርሶ አደሮች ማሳ በበቆሎ ዘር መሸፈኑን የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ግብርና ክፍል ኃላፊ አቶ እሸቱ ጴጥሮስ አስታውቀዋል።

አርሶ አደሮቹ ከወራት በፊት በኩባንያው የኤክስቴንሽን አገልግሎት አማካኝነት መደራጀታቸውን ያወሱት ኃላፊው በጥቂት ጊዜ ውስጥ አበረታች እንቅስቃሴዎች እየታዩ እንደሆነ በማስረዳት ምርቱ ሲሰበሰብም ጥራቱን የጠበቀ የበቆሎ ምርት በበቂ አቅርቦትና በተመጣጣኝ ዋጋ ወደ ገበያ ለማስገባት እንደሚቻል ገልጸዋል።

ምስል በ ኑብዮ ዳንኤል



**“ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አስፈላጊ የሆነ የምርጥ ዘር፣ የማረሻና ምርት መሰብሰቢያ ማሽኖች እንዲሁም ኬሚካሎችን አቅርቦት በመጨመር የኩባንያውን የግብርና ሜካናይዜሽን ግብ እውን ለማድረግ በትኩረት እየሠራ እንደሚገኝ ይህም አርሶ አደሮችን በጥራትና በብዛት እንዲያመርቱ በማስቻል ከአገር ውስጥ አልፎ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት እንዲያቀርቡ ሰፊ በር እንደሚከፍት ነው አቶ እሸቱ የተናገሩት።**

በዚሁ ክልል ጋሳራ ኩዬ ወረዳ ደግሞ ከ200 በላይ በሆኑ ገበሬዎች ማሳ በዘመናዊ መሣሪያ የምንጣሮ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል ያሉት ኃላፊው የምንጣሮ ሥራው ሲጠናቀቅ የተለያዩ ቋሚ ሰብሎች እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬዎች የሚዘሩ ይሆናል ብለዋል።

በተመሳሳይ በበቆጂ በበጋ የምርት ወቅት የተዘራ 25 ሄክታር የስንዴ ምርት ዘመናዊ በሆነ መንገድ በመታጨድ ላይ እንደሚገኝ አቶ እሸቱ አክለው ገልጸዋል። ምርቱ ተሰብስቦ ሲያልቅም ባጠቃላይ 750 ኩንታል ለማግኘት የታቀደ ሲሆን ምርቱ ከከገበሬው ሱቆችና ማቀነባበሪያ በተጨማሪ ለተለያዩ ፋብሪካዎችና ድርጅቶች እንደሚቀርብም አብራርተዋል።

በዘርፉ እየተመዘገበ ያለው ምርትና ምርታማነት ከከተማዋ አልፎ በአገሪቱ የሚስተዋለውን የምርት እጥረት በመቀነስ እና ገበያን በማረጋጋት ረገድ ያለውን ትልቅ አስተዋጽዖ ከግምት ውስጥ ማስገባት  ያስፈልጋል ያሉት ኃላፊው በግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሥራቸውን ከኩባንያው ጋር በጋራ ማሳደግ የሚችሉበትን የግብርና ፍራንቻይዝ ሞዴል አሠራር በመቅረጽ ያስመዘገባቸውን አበረታች ውጤቶች በመጥቀስ በዘርፉ ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን "ኑ አብረን እንሥራ" ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

## የከገበሬውን ታወር ፕሮጀክት አፈጻጸም የሚከታተል መንግሥታዊ ተቋማት የተካተቱበት ኮሚቴ እንዲዋቀር ጥሪ ቀረበ።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በታወር ሼር ሆልደር ሞዴል የአክሲዮን ሥርዓት የሚያከናውናቸውን ተግባራት ክትትል የሚያደርግ ኮሚቴ እንዲዋቀር በቀን 07/10/2015 ዓ.ም በኩባንያው መሰብሰቢያ አዳራሽ በተሰጠው መግለጫ ጥሪ የቀረበ ሲሆን የኮሚቴውም ተግባር ፕሮጀክቱ ሥራ ላይ የሚውልበትን ቦታ ግዢ ክፍያ ክንውን ከመቆጣጠር ጀምሮ እስከ ግንባታው ፍጻሜ ድረስ አስፈላጊውን ሕጋዊ ሒደት ያገናዘበ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግን ያካትታል።

ውሳኔውን ያሳለፈው የኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ባካሔደው አስቸኳይ ስብሰባ ሲሆን ከሚዋቀረው የቲኤስ ኤም ክትትልና ቁጥጥር ኮሚቴ በተጨማሪ የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ትልም እውን እንዳይሆን የተለያየ እኩይ ዓላማ ያላቸው አካላት የሚፈጥሩበትን ፈተና ለማሸነፍ እና ራዕዩን ከግብ ለማድረስ እንዲቻል ኩባንያው በኢትዮጵያዊ የተከበረ ባህላችን መሠረት ሰባት አባላትን ያካተተ የሽማግሌ ኮሚቴም ለማዋቀር መወሰኑንና ለተግባራዊነቱም ሒደቶች መጀመራቸውን በመግለጫው አሳውቋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘም  ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከሚንቀሳቀስባቸው 9 የሥራ ክፍሎች በተጨማሪ የኮንስትራክሽን እና ኢንጂነሪንግ ክፍል በማቋቋም 4 ተጨማሪ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረቱን አድርጎ የሚሠራውን "ከገበሬው ሪል ስቴት" ፕሮጀክት ለማቋቋም መወሰኑን አብስሯል። ይህ ፕሮጀክት በስሩ ከገበሬው ታወር፣ አፎርደብል ሃውሲንግ፣ የከገበሬው መንደር እና የከገበሬው ሪል ስቴት የተሰኙ ክፍላት የሚኖሩት ሲሆን በግብርናው ዘርፍ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየተሠሩ ካሉ በርካታ ሥራዎች ጎን ለጎን ከመሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ የሆነውን የመጠለያ ዋስትና ለማረጋገጥ ለማድረግ ይሠራል።

በቀጣይም የደንበኞቹን ተጠቃሚነት እንደሚያረጋግጥ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የኩባንያውን ባለድርሻ አካላት ማለትም ገበሬውን፣ ባለአክሲዮኖችንና ሸማቹን ማኅበረሰብ ለመጥቀም አዳዲስ መርሐግብሮችን እንደሚያስተዋውቅም በዕለቱ ተገልጿል።

በመጨረሻም በመጀመሪያው ዙር የከገበሬው ታወር አክሲዮን ሽያጭ የታየውን የሁሉም ሠራተኞች ትጋትና አስደናቂ ርብርብ በቀጣይም በሁሉም የሥራ ዘርፎችና ተነሳሽነቶች ቀጥሎ  የድርጅቱ ራዕይ እውን እንዲሆን ሠራተኛው የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ የተጠየቀ ሲሆን እጅግ ከፍተኛ በሆነ ገንዘብ በሚገነባውና ዘርፈ ብዙ ጥቅም በሚያስገኘው ታሪካዊ ግንባታ ላይ በመሳተፍ ሁሉም ኢትዮጲያዊ አሻራውን እንዲያኖር ጥሪ ቀርቧል።

የመግለጫው ሙሉ ቃል ከዚህ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡-

ብሔራዊ የከገበሬው ታወር አጣሪና የአፈጻጸም ክትትል ግብረ ኃይል እንዲመሠረት የቀረበ ጥሪን አስመልክቶ ከፐርፐዝ ብላክ ቦርድ የተሰጠ መግለጫ

ሰኔ 7 ቀን 2015 ዓ.ም

ፐርፐዝብላክ ግሎባል በአሜሪካን ሀገር ከ135 በላይ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራ ወንድምና እህቶቻችን መነሳሳት በጠንካራ የቦርድ አባላት የተቋቋመና የጥቁርን የድህነት አኗኗር ለማቃናት ሕልም ይዞ የተነሣ ዓለም አቀፍ ተቋም ነው፡፡ ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ተቋሙ ሥራውን በአገራቸው እንዲጀምርላቸው ቢፈልጉም የኢትዮጵያን የጥቁር ሕዝብ ተምሳሌትነትና የአፍሪካ እናትነትን በማስቀደም ፐርፐዝ ብላክ ግሎባል ፕሮጀክቶቹን በኢትዮጵያ እንዲጀምር ወስኖ ፐርፐዝ ብላክ ኢትዮጵያ በሚል ጸድቆ በሙተግበር ላይ ይገኛል፡፡

ፐርፐዝብላክ ኢቲኤች ትሬዲንግ ኢ.ማ. በ980/2008 የንግድ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር እና 8/L/AA/3/0024416/2013 የንግድ ምዝገባ ቁጥር እንዲሁም በኢ.ኢ.ፌ.120762/14 ኢንቨስትመንት ፈቃድ ቁጥር በተጨማሪም BL/AA/134/673/4386067/2015 የሪል እስቴት ፈቃድ የተመዘገበ ሲሆን ከተጀመረ ሁለት ዓመት ያልሞላው ቢሆንም የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ በማድረግ ፈጣንና ስኬታማ ተቋማዊ ለውጦችንም ለማሳካት ተችሏል፡፡ በርካታ የሥራ ዕድሎችንም ፈጥሮና አመቻችቶ እየተገበረም ይገኛል፡፡ ለዚህም ተግባሩ በርካታ የዕውቅናና የምስጋና ሽልማቶችን ለማግኘትም ችሏል፡፡

ድርጅቱ የገበሬውን የኑሮ ሁኔታ በተሻለ መልኩ ለመቀየር ገበሬውን በክላስተር በማደራጀትና ወደ ዘመናዊ እርሻ በመቀየር እንዲሁም በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ለሚገኘው መላው ሸማች ማኅበረሰብ መፍትሔ ለማምጣት ገበሬውን ከሸማቹ ማኅበረሰብ ጋር በቀጥታ ማገናኘት፣ ማምረት፣ አግሮ ፕሮሰስ ማካሄድ፣ ኢ-ኮሜርስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የገበያ ትስስር በመፍጠር ገበሬው የልፋቱን ዋጋ እንዲያገኝና ኑሮው የተሻለ እንዲሆን በማስቻል ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ምርትን እጅግ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ በማቅረብ መላው ኅብረተሰብ የኢኮኖሚ እፎይታን እንዲያገኝና በተጨማሪም የኑሮ ውድነትን ታሪክ እናድርግ ብሎ የተነሣ በሕዝብ ባለቤትነት የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው።

ኩባንያችን ፐርፐዝ ብላክ ኢቲኤች ከላይ የተጠቀሱትን እጅግ በርካታ ዕቅዶች ውጤታማ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ካፒታል ለማሰባሰብ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ከገበሬው ታወር የሚባል የ60 ቢሊዮን ብር ፕሮጀክት ነድፎ ታወር ሼር ሆልደር በሚባል መንገድ አክሲዮን ገዢዎችን እጅግ በሚጠቅም መንገድ ለመሸጥ ተዘጋጅቷል። የታወር ሼር ሆልደር ሞዴል በኢትዮጵያ በዓይነቱ እጅግ ልዩ የሆነ ሲሆን አክሲዮን ገዢዎችን በገዙት አክሲዮን መጠን በከገበሬው ታወር ላይ ሪል እስቴት የሚያስጥ ነው፡፡

የታወር ሼር ሆልደር ሞዴልን ድርጅታችን ከስድስት ወር በፊት በታላቅ ዝግጅት በሃያት ሬጀንሲ ሆቴል በይፋ ለህዝብ በማስታወቅ ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን ለዚህ ፕሮጀክት ማስገንቢያ የሚሆን ቦታም ጨረታ በማሸነፍ የመጀመሪያውን ዙር 1000 ኢንቨስተሮች በሃገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በማሰባሰብ ከ1.1 ቢሊዮን ብር በላይ በማሰባሰብ ለግዢው ማስፈጸሚያ የሚሆነውን ክፍያ በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ለመፈጸም ዝግጅቱን እያጠናቀቀ ይገኛል።

ይህ በእንዲህ እያለ ይህ የግዢው ክፍያ እንዳይከፈልና ድርጅታችን ያቀደውን ለሃገራችንና ለአህጉራችን እጅግ ትሩፋት የሚኖረው ፕሮጀክት እንዳይሳካ የሚፈልጉና ቦታውን ለራሳቸው በኃይል ለመንጠቅ የሚፈልጉ ሦስተኛ ወገኖች ያለ የሌለ ኃይላቸውን በመጠቀም ተቋማችን ሕዝቡን በማጭበርበር እየዘረፈ እንደሆነ የሚገልጽ የተቀነባበረና የተቀናጀ የስም ማጥፋትና ተቋሙን የማጥላላት በገንዘብ የተደገፈ ዘመቻ ጀምረዋል። ከዚያም አልፎ ተቋሙ ከጨረታው እራሱን እንዲያገል ከማስፈራራት ጀምሮ የተቋሙን ኃላፊዎች ማስፈራራትና ሌሎችም የተቋሙን ህልውና የሚፈታተኑ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ ጀምረዋል።

የፐርፐዝ ብላክ ቦርድም የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳትና የተቋሙን ከ20,000 ባለ አክሲዮኖች ጥቅም እንዲሁም የተቋሙን በሺዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞች ህልውና የተፈታተነውን ጉዳይ በጥሞና ከተወያየ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ውሳኔዎች ወስኗል።

1. በተቋሙ ላይ በተቀነባበረ ሁኔታ የተነሳውን የተአማኒነት ጥያቄ በተመለከተ ከእንግዲህ በኋላ ፕሮጀክቱ ተገንብቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ የከገበሬው ታወር ፕሮጀክት ከተለያዩ የመንግሥት የሚንስትር መሥሪያ ቤቶችና ሌሎችም ሕዝባዊ ተቋማት የተውጣጣ ግብረ ኃይል አጣሪነትና ተቆጣጣሪነት እንዲመራ ተወስኗል። በግብረ ኃይሉም እንዲሳተፉ የተጋበዙት ተቋማት የሚከተሉት ናቸው፤

1.1. የግብርና ሚንስቴር
1.2. የንግድና ቀጠናዊ ትሥሥር ሚንስቴር
1.3. የፍትሕ ሚንስቴር
1.4. የገንዘብ ሚንስቴር
1.5. የገቢዎች ሚንስቴር
1.6. የጸረ ሙስና ኮሚሽን
1.7. የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ
1.8. የፋይናንስ ደኅንነት አገልግሎት
1.9. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለስልጣን
1.10. የሸማቾች ሙብት ጥበቃ ኤጀንሲ
1.11. የኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ ተቋም
1.12. በአዲስ አበባ መስተዳድር የመሬት አስተዳደር
1.13. የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
1.14. የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማኅበር
1.15. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
1.16. አቢሲንያ ባንክ
1.17. አዋሽ ባንክ

2. ግብረ ኃይሉም የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል
2.1. ሰሞኑን በተቋሙ ላይ ያነጣጠሩትን ውንጀላዎች ተዓማኒነት ያጣራል እርምት መወሰድ ያለባቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያስተላልፋል
2.2. የቦታውን ግዢ ሂደት በማጣራት የግዢ ክፍያው ባስቸኳይ እንዲፈጸም ሁኔታዎችን ያመቻቻል
2.3. የባለአክሲዮኖች ሙብቶች መጠበቃቸውን ይከታተላል
2.4. ለከገበሬው ፕሮጀክት መሳካት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል
2.5. ፕሮጀክቱን በተመለከተ ለሕዝብ የሚቀርቡትን ማስታወቂያዎች ተአማኒነት ያጣራል
2.6. ፕሮጀክቱ በታቀደለት መንገድ እየተጓዘ መሆኑን ይከታተላል
2.7. ስለ ፕሮጀክቱ ሒደት በየሦስት ወር ለሕዝብ ሪፖርት ያቀርባል

3. ግብረ ኃይሉም በግብርና ሚንስቴርና በንግድና ቀጠናዊ ትሥሥር ሚንስቴር ጥምር ሰብሳቢነት በየወሩ የሚሰበሰብ ሲሆን በቅድሚያ የሚያከናውናቸው ተግባራት
3.1. ሰሞኑን ከአክሲዮን ሽያጩ ጋር ተከሰቱ የተባሉትን ክሶችና ሌሎች ችግሮች አጣርቶ መፍትሔ ይሰጣል
3.2. የቦታውን ግዢ አጣርቶ የግዢው ክፍያ ባስቸኳይ እንዲከፈል ጥሪት ያደርጋል

4. ግብረ ኃይሉ ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች እያከናወነ እያለ በተጓዳኝ ሰሞኑን የተከሰቱት አላስፈላጊ ግጭቶችን በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ይፈቱ ዘንድና ሁኔታዎች ወደ አልተፈለጉ አቅጣጫዎች እንዳይዞሩ የሚሸመግል 7 አባላት የሚገኙበት ቋሚ የሽምግልና ቡድን የተቋቋመ ሲሆን ቡድኑም ሁሉንም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላትና ባለድርሻዎች በማነጋገር ሁኔታዎች ሰክነው የፕሮጀክቱ እንቅስቃሴ ያለእንከን እንዲከናወን ጥረት ያደርጋል

Purpose Black ETHIOPIA

5. የፐርፐዝ ብላክ ቦርድ ይህ በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ገበሬዎች እንዲሁም በሺዎች ለሚቆጠሩ የድርጅቱ ሠራተኞች ሕልውና እንዲሁም ለሃገራችን አልፎም ለአህጉራችን ታላቅ ትሩፋት ያለው ፕሮጀክት በግልጽነት፣በፍትሕ፣ በተጠያቂነትና በአብሮ መሥራት መርሕ በውጤት ይሳካ ዘንድ በራሱ በኩል እጁን በመዘርጋት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በሒደቱ ተሳታፊ ይሆኑ ዘንድ በፍጹም ኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ግልጽነት ጋብዟል፣ የራሳችንን ኃላፊነት በመወጣት በሕዝብ ፊት ሁኔታዎች በግልጽ አስቀምጠን ፕሮጀክቱ ይሳካ ዘንድ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥሪ ያስተላለፍን ሲሆን ላቀረብነው ጥሪ የተሰጠውን ምላሽና የፕሮጀክቱን ሒደት በተከታታይ ለሕዝብ የምናሳውቅ ይሆናል።

የፐርፐዝ ብላክ ቦርድ
ሰኔ 7 ቀን 2015 ዓ.ም

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በአገራችን ወደተግባር ገብቶ የመማከርት ጉባኤ ካቋቋመ ሁለተኛ ዓመቱን አስቆጠረ።

እ.አ.አ. በ2020 የጥቁር አሜሪካዊውን ጆርጅ ፍሎይድ የግፍ ግድያ ተከትሎ የተነሣው "Black Lives Matter" የተሰኘ የጥቁሮችን መገለል እና ግፍ የሚያወግዝ እንቅስቃሴ በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ በድሉ አድራጊነት የነጻነት ጮራን ፈንጥቃ ለአፍሪካውያንና ለመላው ጥቁር ሕዝብ ተምሳሌት ከሆነችው ኢትዮጵያ አብራክ የተገኙት ልጆቿን በዓድዋ የነጭ ወራሪን አሳፍረው ባባረሩት አባቶቻቸው ወኔ እስከመቼ የጥቁር ማኅበረሰብ ኢፍትሐዊነትን፣ እንግልትን፣ እና መገለልን ተሸክሞ ይኖራል ብለው እንዲነሡ በውጤቱም የማይቀለበስ ዘላቂ መፍትሔ ለማበጀት በቆራጥነት መንቀሳቀስ እንዲጀምሩ ምክንያት ሆነ።

የዚህ ጽንሰ ሐሳብ አመንጪ በአገራችን ኢትዮጵያ የግል የትምህርት ተቋማት ፈር ቀዳጅ የሆነው የቀድሞው ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ መሥራች እና ባለቤት ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ሲሆኑ እንቅልፍ ያሳጣቸውን ይህን የጥቁር ሕዝብ ዘር ተኮር ስቃይና መከራ የማስቆም ውጥን ለቅርብ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወዳጆቻቸው ማጋራት ጀመሩ።

ውጥኑም ወደ ውይይት አድጎ በጥቁርነት የሚደርሰው ጫና፣ መገለል፣ አድሏዊነት፣ ግፍ፣ እና እንግልት እስከመቼ ይዘልቃል የሚለውን ዶ/ር ፍስሐን እና ባልደረቦቻቸውን እረፍት የነሳ ቁጭታዊ ጥያቄ ምላሽ መስጠትን ዓላማ አድርጎ መካሔድ ቀጠለ። ይህም ጥያቄ እንደ ዜጋ ምን በጎ አስተዋጽዖ ማበርከት እንችላለን ብለው ወደ አንድ የመፍትሔ አቅጣጫ እንዲደርሱ እና "Black Economy Excellence" የተሰኘውን ተነሣሽነት ለመመሥረት መንገድ ከፈተላቸው።

"Black Economy Excellence" በዓለም ላይ ከ1.3 ቢሊዮን በላይ የሚሆነውን ጥቁር ማኅበረሰብ በፖለቲካዊ ተቃውሞ ለክፍላተ ዘመናት የዘለቀውን የጥቁር ነጻነት የማረጋገጥ እንቅስቃሴ በኢኮኖሚያዊ መንገድ በሚሰፍን ልዕልና ለሙተካት ታላቅ ራዕይን አንግቦ ወደ ተግባር ገባ። "Black Economy Excellence" ጥቁሮችን በኢኮኖሚው ዘርፍ ራሳቸውን እንዲችሉ ከዚያም ባለፈ ሰብዓዊ ክብርና ልዕልናቸውን እንዲያረጋግጡ የሚያስችል እና በፍላጎት እና ትብብር ለመሥራት የሚረዳ መድረክ ሆነ።

ለኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው መሠረትና ግብአት የሚሆነው ተፈጥሯዊ ሀብት የተትረፈረፈላት አፍሪካ የአብዛኛው ጥቁር ማኅበረሰብ መገኛ እንደመሆኗ "Black Economy Excellence" ም በዚህች አህጉር መሠረቱን ማድረግ እንዳለበት መሥራቾቹ ወሰኑ።

"Black Economy Excellence" አፍሪካን ማእከል እንዲያደርግ የተቀመጠው አቅጣጫም በአህጉሪቱ አብዛኛው ማኅበረሰብ በገጠራማ ክፍሎች በግብርና እየተዳደረ የሚኖር እንደመሆኑ እንቅስቃሴውም በገጠራማ አካባቢዎች የሚከናወነውን ግብርና እና ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ መሆን እንደሚገባው ታምኖበት ውጥኑ እውን የሚሆንበትን አገር ወደመምረጥ ሒደት ተሸጋገረ።



በአፍሪካ መሠረቱን አድርጎ እንዲንቀሳቀስ ውሳኔ ተላልፎለት ለውጥኑ እውን መሆን ሩዋንዳንና መሰል የአህጉሪቱን አገራት መነሻ ለማድረግ አማራጭ የያዘውን "Black Economy Excellence" በነጻነት ተምሳሌትነቷ የተነሳሽነቱን ራዕይ እውን ለማድረግ አንጻር አዎንታዊ ሚና እንዲሁም የሐሳቡ አመንጪዎች ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው አገራችን የዚህ ታላቅ ሐሳብ ትግበራ መነሻ እንድትሆን ተመረጠች።

በገጠራማ የአፍሪካ አካባቢዎች ግብርናን እና ቴክኖሎጂን ማእከል አድርጎ ለመንቀሳቀስ በሐሳብ የቆየውን "Black Economy Excellence" የተሰኘ ጽንሰ ሐሳብ ለማዋለድ የተቋቋመው ተቋም ደግሞ ፐርፐዝብላክ ተብሎ ተሰየመ።

ለአንድ ዓመት ያህል በጥንስስ የዘለቀው "Black Economy Excellence" በአገራችን በተግባር በዋለ በ7 ወራት ጊዜ ውስጥም ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የተሰኘው ተቋም ኢትዮጵያን ማእከል አድርጎ ተቋቋመ።

ይህ በአብዛኛው በአፍሪካ ገጠራማ አካባቢ የሚገኘውን እና ግብርናን መተዳደሪያ ያደረገ ጥቁር ማኅበረሰብ ሕይወት ለመቀየር የተቋቋመው ኩባንያችን ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በአገራችን ተመሥርቶ ሰኔ 8 ቀን 2013 ዓ.ም በይፋ የመማከርት ጉባኤ አቋቋመ።

የገበሬውን ሕይወት መቀየርን እና በአገራችን የኑሮ ውድነትን ታሪክ በማድረግ የጥቁርን ሕዝብ በኢኮኖሚያዊ ልዕልና ወደቀደመ ክብሩ ለመመለስ የተነሳው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ ቴክኖሎጂን መሠረት ባደረጉ ፕሮጀክቶች ወደ ተግባር ገብቶ የመማከርት ጉባኤ ካቋቋመ እነሆ 2ኛ ዓመቱን አስቆጠረ።

## ፐርፐዝብላክ ሚዲያ ለኩባንያው መልካም ገጽታ ግንባታ ጉልህ አስተዋጽዖ እንደሚያበረክት ተገለጸ።

ፐርፐዝብላክ ሚዲያ እውነተኛ እና ሚዛናዊ መረጃዎችን በማጋራት የኩባንያውን መልካም ስምና ገጽታ በመገንባት ረገድ ትልቅ ሚና እንዳለው የኩባንያው ቺፍ ኦፍ ስታፍ አቶ ተፈራ ኃይሉ ገልጸዋል።

የፐርፐዝብላክ ሚዲያ ክፍል በዋናነት የኩባንያውን ሥራ ክንውን እና ሁነቶች በመዘገብ እንዲሁም ምርትና አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ኩባንያውን የተመለከቱ መረጃዎችን ተደራሽ እያደረገ የሚገኝ ሲሆን ከኩባንያው የትስስር ገጾች በተጨማሪ የተለያዩ ወቅታዊ መረጃ እና ማስታወቂያዎችን በቴሌቪዥን እና ሬዲዮ ጣቢያዎች እንደሚሰራጭ ኃላፊው አብራርተዋል።

“

**የኩባንያው የሚዲያ ክፍል ኃላፊ አቶ ዋሲሁን ዋጋው በበኩላቸው ክፍሉ ዩቲዩብና ፌስቡክን ጨምሮ በተለያዩ የማኅበራዊ ትስስር ገጾች እንዲሁም በተመረጡ የሕትመት አማራጮች መረጃዎችን ሲያሰራጭ የቆየ መሆኑን በማስታወስ በቅርቡም ከገበሬው የተሰኘ የቴሌቪዥን ጣቢያ ለመክፈት TCTዝብላክ ኢቲኤች ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ፈቃድ ማግኘቱንና በይዘትና በዓይነት የተለያዩ መሰናዶዎችን በማካተት ተደራሽነቱን ይበልጥ ለማስፋት እንቅስቃሴዎችን መጀመሩን አስታውቀዋል።**

**ይህም የሕብረተሰቡን መረጃ የማግኘት መብት ከማረጋገጥ ባሻገር ሙያዊ ስነ-ምግባርን በተላበሰ አቀራረብ ትክክለኛ፣ ሚዛናዊ፣ ተአማኒነትና ተጨባጭነት ያለው መረጃ በማቀበል ዜጎች በመረጃ የተደገፈ ምርጫ እና ውሳኔ እንዲኖራቸው ያስችላል ነው” ያሉት ኃላፊው።**

በአሁኑ ሰዓት ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በዩቲዩብ፣ ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ሊንክድ ኢን፣ ኢንስታግራምና ትዊተር ገጾች አማካኝነት በርካታ ተከታዮችን ማፍራት የቻለ ሲሆን ይህ መረጃ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በዩቲዩብ ገጽ ብቻ ከ10 ሺህ በላይ ተከታዮችን ማፍራት መቻሉም ተገልጿል።

በቀጣይም ለኩባንያው አመራርና ሠራተኞች፣ ባለአክሲዮኖች፣ በአጋርነት ለሚሠሩ አካላት እንዲሁም ከፐርፐዝብላክ ጋር አብሮ ለመሥራት ፍላጎት ላላቸው አካላት ራዕዩን በጥልቀት በማስረዳት ኩባንያውን የማስተዋወቂያ መንገዶችን እንደሚያመቻች የክፍሉ ኃላፊ አስታውቀዋል።

PURPOSE BLACK MEDIA

**ዋና አዘጋጅ፦ ሰላማዊት ደበበ**
**ሲንየር ሪፖርተር፦ ጌታባለው ገ/ሐና**
**ሪፖርተር፦ ኤደን ደነቀ**

## ለበለጠ መረጃ

ስንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ
+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222
7151
www.purposeblackethiopia.com